# ዳኝነት እንደገና ስለሚታይበት ሁኔታ(Review of judgement)                    ተጠምቀ ዮሐንስ

አንድ ክስ ለፍርድ ቤት ያቀረበ ወገን ተገቢዉን ክርክር ከባለጋራዉ ጋር ካደረገ በኃላ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ ዉሳኔ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በዉሳኔዉ ቅር የተሰኘ ወገንም በየደረጃዉ ለሚገኙ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ይግባኙን በማቅረብ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ እንዲሻሻል፣እንዲሻር መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ስ/ስ/ህግ 320 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌወች በማየት መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ራሱ በድጋሚ አይቶ የሰጠዉን ፍርድ ወይም ዉሳኔ የሚያሻሽልበት ስርዓትም እንደዚሁ በስነ ስርዓት ህጉ ላይ ተቀምጦ ይገኛል፡፡ በዚህ አጭር ጽሁፍ ዉሳኔ በሰጠዉ ፍርድ ቤት( court of rendention) ዳኝነት እንደገና ስለሚታይበት ሁኔታ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ አንድ ፍርድ ወይም ወሳኔ የሰጠ ፍርድ ቤት የራሱን ዉሳኔ ወይም ፍርድ በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ድጋሚ አይቶ ሊያሻሽል ወይም ሊለዉጥ ይችላል፡፡ እነዚህም የስነ-ስርዓት ግድፈቶች(procedural irregularities) ሲኖሩ አዲስ ማስረጃ ሲገኝ(newly discovered evidence) እና ተቃዉሞ( opposition) ሲቀርብ ናቸዉ፡፡

<u>**የስነ-ስርዓት ግድፈቶች(procedural irregularities**</u>) የምንለዉ በየእለቱ የችሎት ስራወች ላይ ከሚሰሩ ስህተቶች ወይም በቀላሉ ሊታረሙ ከሚችሉ የስነ-ስርዓት ግድፈቶች የተለዩ ናቸዉ፡፡ ለምሳሌ በመጥሪያ፣ብይን፣ትዕዛዝ፣ፍርድ ላይ የቀን፣ የቁጥር እና ሌሎች የሂሳብ ስህተቶችን ፍርድ ቤቶች በመዝገቡ ላይ ባገኙ ጊዜ በራሳቸዉ አነሳሽነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች አመልካችነት ወዲያዉኑ ሊያስተካክሉ ወይም ሊያርሙ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 208 ይገላጻል፡፡ እነዚህም ስህተቶች ሲታረሙ የስነ ስርዓቱን ዋናዉን አካሄድ የማይነኩ ( do not affect the validity of the proceedings) ስለሆነ ዳኝነት እንደገና እንዲታይ የሚያደርጉ የስነ-ስርዓት ግድፈቶች(procedural irregularities) የሚባሉ አይደሉም፡፡ የስነ ስርዓት ግድፈት የምንለዉ ፍርድ ቤቱ በሰጠዉ ፍርድ ወይም ዉሳኔ ላይ ቀጥተኛ ዉጤት ያላቸዉ እና ስህተቱ ባይፈጸም ኖሮ ዉሳኔዉ ወይም ፍርዱ አይሰጥም ነበረ የሚያስብሉ መሆን አለባቸዉ፡፡ ፍርድ ቤቶችም እንደዚህ አይነት ስህተት መፈጸሙን ሲያዉቁ በራሳቸዉ አነሳሽነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች አቤቱታ መሰረት ጉዳዩን በድጋሚ አይቶ የሰጡትን ፍርድ ወይም ዉሳኔ ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡ ስህተቱ መፈጸሙን ክርክሩ በሚደረግበት ወቅት ፍርድ ቤቱ የተረዳ እንደሆነ ወይም በተከራካሪወች ተቃዎሞ ቀርቦ ከሆነ ወዲያዉ ሊያርም የሚገባ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ስህተቱ የታወቀዉ ፍርድ ወይም ወሳኔ ከተሰጠ በኃላ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በስህተት ፍርድ እንዲሰጥ ያስደረገዉ ምክንያት መኖሩን አረጋግጦ ስህተቱን በማስተካከል የሰጠዉን ፍርድ ወይም ዉሳኔ ሊያሻሽል ወይም ቀሪ ሊያደርግ የሚገባ ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ በኃላም ክርክሩ ሊቀጥል የሚገባ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳ ቀደም ሲል የተሰጠ ፍርድ ወይም ወሳኔ ቀሪ መሆኑን ተከራካሪ ወገኖች እንዲያዉቁት አድርጎ ክርክሩን ማስቀጠል አለበት፡፡ ከዚያም ተገቢዉ ክርክር ከተደረገ እና ማስረጃ ከተሰማ በኃላ ዉሳኔ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ፍርድ ቤቶችም በሰጡት ፍርድ ወይም ዉሳኔ ላይ የስነ-ስርዓት ግድፈት አለ በማለት የሰጡትን ፍርድ ወይም ዉሳኔ ከማስቀረታቸዉ በፊት የስነ ስርዓት ግድፈት ተፈጽሟል ተብሎ የሚቀርብ አቤቱታ ተገቢነት በሚገባ መመርመር አለባቸዉ፡፡

**አዲስ ማስረጃ ሲገኝ(newly discovered evidence)** ይህ አይነቱ ምክንያት በብዛት ዳግም ዳኝነት እንዲታይ በሚቀርቡት አቤቱታወች ላይ የተለመደ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቶች እንዲህ አይነቱ ምክንያት ሲቀርብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 6 ላይ ከተቀመጡ ነጥቦች አንጻር በሚገባ መመልከት አለባቸዉ፡፡ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 6. 1 (ሀ) የመጨረሻ ፍርድ ወይም ወሳኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠዉ በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበዉን ሰነድ ወይም ሀሰተኛ የምስክርነት ቃልን፣ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሰረት በማድረግ ሲሆንና አቤት ባዩም ፍርድ ከመስጠቱ በፊት አስፈላጊዉን ትጋት አድርጎ ለማወቅ ያለመቻሉን ለማስረዳ የቻለ እንደሆነ እንዲሁም እነዚህ ተግባሮች መፈጸማቸዉ ቢገለጽ ኖሮ ለፍርዱ መለወጥ ወይም መሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችሉ እንደነበረ ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ እና በዉሳኔዉ ላይም ይግባኝ ያልተባለበት መሆኑን (ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ/ቁ 43821 ላይ ይግባኝ የተባለ ቢሆንም እንደገና ዳኝነት እንዲታይ መጠየቅ የሚቻል ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ስጥቷል) መግለጽ የሚገባ እንደሆነ ፍርዱ ዳግም እንዲታይ ለፈረደዉ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ እንደሚቻል ያደነግጋል፡፡ እዚህ ጋር ልብ ሊባል የሚያስፈልገዉ አዲስ ማስረጃ ስለተገኘ ብቻ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በድጋሚ ሊያዩ እንደማይገባ ነዉ፡፡ አዲስ ማስረጃ ተገኝቷል የሚል ወገን ማስረጃዉ የተገኘዉ ዉሳኔ ከተሰጠ በኃላ እንደሆነ፣ አዲስ የተገኘዉ ማስረጃ ክርክሩ በሚደረግበት ጊዜ ቢገለጽ ኖሮ ዉሳኔዉ ላይ የተለየ ዉጤት የሚያመጣ ስለመሆኑ እና ማስረጃዉ በተጭበረበረ መንገድ ወይም በሀሰት የተገኘ ስለመሆኑ ማስረዳት አለበት፡፡ ፍርድ ቤቶችም እነዚህ ሁኔታዉች መኖራቸዉን ሲያረጋግጡ አንድን ክርክር በድጋሚ የሚያዩ ይሆናል፡፡ የዳግም ዳኝነት አቤቱታም መቅረብ ያለበት አዲስ ማስረጃ በተገኘ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቱም አቤቱታዉን የተቀበለ እንደሆነ ለተቃራኒ ወገን ተገቢዉን መጥሪያ አድረጎ ክርክሩን የሚያስቀጥል ይሆናል፡፡

**ተቃዉሞ( opposition)** ፍርዱን በሰጠዉ ፍርድ ቤት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ የሚያደርግ ሶስተኛዉ ምክንያት በተሰጠዉ ፍርድ ወይም ዉሳኔ ላይ ተቃዉሞ ሲቀርብ ነዉ፡፡ ይህም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 358 መሰረት የአንድ ክርክር ተከፋይ መሆን ሲገባዉ ያልተከራከረ ወገን በክርክሩ ምክንያት የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቱን ወይም ጥቅሙን በሚነካበት ጊዜ የተሰጠዉን ፍርድ ወይም ዉሳኔ በመቃወም የሚያስለዉጥበት ስርዓት ነዉ፡፡ በሌላ አባባል የፍርድ ተቃዉሞ የሚቀርበዉ ቀደም ሲል በነበረዉ ክርክር መከራከር ሲገባዉ ያልተከራከረ ወገን የክርክሩ ተከፋይ ባለመሆኑ የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቱን ሲጎዳ ነዉ፡፡ የፍርድ ተቃዉሞ የሚያቀርቡ ተከራካሪወችም ክርክሩ ላይ የግድ ተካፋይ መሆን የነበረባቸዉ ( indispensable parties)፣ ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ ጥቅም ያላቸዉ እና በዉሳኔዉ ጥቅማቸዉ የተነካባቸዉ ግለሰቦች ናቸዉ፡፡ ፍርድ በቶችም እነዚህ ግለሰቦች የሚያቀርቡትን አቤቱታ በሚገባ ከመረመሩ በኃላ የቀረበዉ ተቃዉሞ አግባብነት እንዳለዉ ያመኑ እንደሆነ በመደበኛዉ ስርዓት መሰረት መዝገቡን በማየት የግራ ቀኙን በማከራከር እና ማስረጃ በመስማት ቀደም ሲል የሰጡትን ፍርድ ወይም ዉሳኔ ሊያስቀሩ፣ሊያሻሽሉ ያችላሉ፡፡ ከዚህ ጋር መታወቅ ያለበት ጉዳይ የፍርድ ተቃዉሞ የሚያቀርበዉ ወገን ቀደም ሲል ክርክሩ ሲደረግ የሚያዉቅ የነበረ ከሆነ ምን ሊሆን ይገባል? ፍርድ ቤቶችስ እንዲህ አይነት ተከራካሪወች የሚያቀርቡትን ተቃዉሞ ሊቀበሉ ይገባል ወይ? ስንል የስነ ስርዓት ህጉ ክርክሩ ላይ የግድ ተካፋይ መሆን የነበረባቸዉ (indispensable parties) ከሆኑት ዉጭ ሌሎች ተከራካሪወች ቀደም ሲል ክርክሩ ሲደረግ እያወቁ ሳይከራከሩ ቀርቶ ፍርድ ከተሰጠ በኃላ የሚያቀርቡትን ተቃዉሞ መቀበል የፍርድ ሂደት የሚያጓትት እና የስነ ስርዓት ህጉን ዓላማ የማያሳካ ስለሆነ ተቃዉሞን መቀበሉ ተገቢነት የለዉም በማለት አቤቱታወችን ወድቅ ሲያደረጉ ይስተዋላል፡፡ ይህም በሁለት ምክንያቶች ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡ የመጀመሪያዉ አንድ ተከራካሪ ክርክሩ ሲደረግ ያዉቅ ነበረ ለማለት

የሚያስችል በቂ ምክንያት ወይም ደረጃ (standard) ያልተቀመጠ በመሆኑ በቀላሉ ማወቅ የማይቻል ሲሆን ሁለተኛዉ በስነ ስርዓት ህጉ በግልጽ ድንጋጌ ባልተቀመጠበት ሁኔታ ቀደም ሲል ክርክሩ ሲደረግ እዉቅናዉ እያለህ ቀርበህ አልተከራከርክም በማለት ተቃዉሞን ዉድቅ ማድርግ ተገቢ ባለመሆኑ ነዉ፡፡ በመሆኑም የፍርድ ተቃዉሞ አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች እንደነገሩ ሁኔታ አቤቱታዉን በሚገባ በመመልከት የስነ ስርዓት ህጉን ዓለማ በሚያሳካ መልኩ ሊያስተናግዱ የሚገባ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተገለጹ ሶስት ምክንያቶች አንድ ፍርድ ወይም ዉሳኔ ፍርዱን በሰጠዉ ፍርድ ቤት ድጋሚ ዳኝነት የሚታይ ይሆናል፡፡